# <u>የፖፕ ፓየስ 11ኛና የፋሺሽቶች ሕብረት</u>

በኪዳኔ ዓለማየሁ

## <u>መግቢያ፤</u>

የኢጣልያ ፋሺሽቶች፤ በቫቲካን ያልተቆጠበ ድጋፍ፤ ኢትዮጵያን በወረሩባቻው አምስት ዓመቶች፤ እጅግ ብዙ የጦር ወንጀሎች ፈጽመው ነበር። ከነዚያም ውስጥ፤ በብዙ ማስረጃዎች ተረጋግጠው የሚገኙት፤

1ኛ/ አንድ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያንን፤ ከብዙ አውሮፐላኖች በተነሰነሰ የመርዝ ጋዝ፤ በጥይት፤ በቦምብ፤ በእሳት በማቃጠል፤ በመስቀል፤ **ከአውሮፐላን በመወርወር፤** ወዘተ. ጨፍጭፈዋል። ከነዚሁ ውስጥ፤ በአዲስ አበባ ብቻ፤ በሶስት ቀኖች፤ 30 000 ሰዎች፤ በተጨማሪም፤ በደብረ-ሊባኖስ ገዳም፤ 1000 መነኮሳት፤ እንዲሁም አቡነ ጴጥሮስና አቡነ ሚካኤል፤ ተገድለዋል።

2ኛ/ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን፤ በእሥርና በልዩ ልዩ ሰቆቃዎች፤ የመከራና የፍዳ ዘመን አሳልፈዋል።

3ኛ/ 2 000 ቤተ ክርስቲያኖች፤ 525 000 ቤቶች፤ 14 ሚሊዮን እንስሶች ከመውደማቸው በላይ፤ በተነሰነሰው የመርዝ ጋዝ፤ ሰፊ የአካባቢ ብክለት ተከስቶ ነበር።

ሆኖም፤ በአርበኞቻችን ያላሰለሰ ትግል፤ በሕዝቡ መስዋእትነትና በወዳጅ ሐገሮች እርዳታ፤ ፋሺሽቶቹ ተወግደው፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ነጻነታችንን ብንጎናጸፍም፤ በሐገራችን ላይ ለተፈጸመው አሰቃቂ ግፍ እስካሁን ድረስ በቂ የሆነ ካሣ ስላልተከፈለ፤ ዓለም-አቀፍ ሕብረት ለፍትሕ - የኢትዮጵያ ጉዳይ፤ (Global Alliance for Justice – The Ethiopian Cause) www.globalallianceforethiopia.org) የተሰኘው ድርጅት፤ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ዓላማዎች እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፤

1ኛ/ በፖፕ ፓየስ 11ኛና 12ኛ ትመራ የነበረችው ቫቲካን፤ ከፋሺሽቶች ጋር በመተባበሯ፤ ጦሩንም በመባረኳ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ፤ (ይህንን ዓላማ በተመለከተ፤ ከላይ በተጠቀሰው የድርጅቱ ድረ-ገጽ እንደሚታየው፤ ቫቲካን የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ የሚያሳስበው ዓለም-አቀፋዊው አቤቱታ፤ እስካሁን ድረስ፤ ከ30 ሐገሮች በላይ የሚገኙ፤ 3 570 ዜጎች ፈርመውታል። የዚህ ጽሑፍ አንባቢዎችም ዓላማውን በመደገፍ አቤቱታውን፤ በድረ-ገጹ ላይ ሊፈርሙ ይችላሉ።)

2ኛ/ ፋሺሽቶች ለፈጸሙት ወንጀል፤ የኢጣልያን መንግሥት፤ የቆቃ ግድብን ለማሠሪያ የከፈለው፤ 6 ሚሊዮን ስተርሊንግ ፓውንድ፤ በተለይ ለሊቢያ ለመክፈል ከተስማማችው፤ ከ$5 ቢሊዮን፤ ጋር ሲወዳደር በምንም መስፈርት ሲታሰብ በቂ ስላልሆነ ተገቢውን ካሣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንድትከፍል፤

3ኛ/ በቫቲካንና በኢጣልያኖች እጅ የሚገኙ ከኢትዮጵያ የተዘረፉ ንብረቶች እንዲመለሱ፤

4ኛ/ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፤ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመውን የጦር ወንጀል፤ በታሪክ ሰነዱ እንዲያውል፤

5ኛ/ በቅርቡ፤ እ.ኤ.አ. ነሐሴ 11 ቀን 2012፤ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመውን ግፍ ይመራ ለነበረው፤ ወንጀለኛ፤ ለሮዶልፍ ግራዚያኒ፤ አፊሌ በምትሰኝ፤ ከሮም ወደ ደቡብ በምትገኝ ከተማ፤ **የቫቲካን ተወካይ በተገኙበት፤** የተመረቀለት መካነ-መቃብርና መናፈሻ እንዲፈርስ ለማድረግ ነው።

ድርጅቱ፤ ከላይ የተጠቀሱትን ዓላማዎቹን ለማስገኘት፤ ዘርፈ-ብዙ ተግባሮችን እያከናወነ ይገኛል። ሰሞኑን ግን፤ አንድ ያልታሰበና ያልተጠበቀ ክስተት አጋጠመው። ይኸውም፤ የቀድሞ አምባሳደር፤ አቶ ዘውዴ ረታ፤ "የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት" በተሰኘው መጽሓፋቸው፤ ፋሺሽቶች በኢትዮጵያ ላይ ለፈጸሙት እጅግ ከባድ የጦር ወንጀል፤ በጊዜው የነበሩት፤ የቫቲካን መሪ፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛ ተጠያቂነት የለባቸውም በማለት ስለ ዘገቡ፤ በተቃራኒው፤ እኚሁ ፖፕ፤ ከፋሺሽቶቹ፤

በተለይም ከሙሶሊኒ ጋር እጅና ጓንት ሆነው ይሠሩ እንደ ነበር የሚያረጋግጡ፤ ከታሪክ ማሕደሮችና ከልዩ ልዩ ምሑራን ከተገኙ አስተማማኝ ማስረጃዎች በዚህ ጸሓፊ አማካኝነት፤ በይፋ ቀርበዋል። ዝርዝሩን፤ ከዚህ በታች በተመለከተውና ctrl ላይ በመጫን መመልከት ይቻላል፤

[Complicity Between the Vatican and the Fascists.pdf]

ቅዳሜ፤ ጥቅምት 5 ቀን 2005 ዓ/ም፤ ኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ፤ በተከናወነው የመጽሐፋቸው ፍረማ ሥርዓት ባረጋገጡት መሠረትና ቀደም ብለውም፤ በ9/26/12፤ በእጃቸው በጻፉት ደብዳቤ መሠረት፤ ፖፕ ፓየስ ፋሺሽቶችን መባረካቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካገኙ፤ በመጽሓፋቸው የዘገቡትን ለማስተካከል ዝግጁ መሆናቸውን አቶ ዘውዴ ረታ ገልጸዋል። ይህንኑ መሠረት በማድረግ፤ ግልጽ የሆኑ ማስረጃዎች፤ ከዚህ ቀጥሎ ይቀርባሉ። በዚህ አጋጣሚ፤ ደራሲው፤ በመጽሓፋቸው ውስጥ ያካተቱት ዘገባ፤ በአብዛኛው፤ ከቫቲካን ባገኙት ማስረጃ በመሆኑ፤ በተጨማሪ የቀረቡላቸውን ሰነዶች በጥንቃቄ ተመልክተው፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛና ቫቲካን ፋሺሽቶችን ደግፈው የነበሩ መሆኑን የሚያረጋግጥ መግለጫ ለማውጣት ዝግጁ በመሆናቸው ልዩ ምሥጋና ይገባቸዋል።

የዚህ ጦማር መሠረታዊ ዓላማም፤ ቫቲካን፤ ከፋሺሽቶች ጋር በመተባበር በሐገራችን፤ በኢትዮጵያ ላይ ለደረሰው እልቂትና ውድመት፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ እንድትጠይቅ ለማድረግ ሲሆን፤ አቶ ዘውዴም፤ የአምባሳደርነት፤ የደራሲነትና የሌላም ሰፊ ተሞክሯቸውንና ችሎታቸውን፤ ለሐገራችን ፍትሕና ክብር እንደሚያውሉት በማመን ነው። ለዚህም ዓላማ፤ <u>ስለ ፖፕ ፓየስ 11ኛ በመጽሓፋቸው ያካተቱትን ዘገባ፤ በጽሑፍ፤ በይፋና በፍጥነት በማስተካከል፤ ለኢትዮጵያ ጠላቶች መጠቀሚያ እንዳይሆን ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ ለማሳሰብ ነው።</u>

## <u>ፖፕ ፓየስ ፋሺሽቶችን ስለ መባረካቸውና መደገፋቸው የቀረቡ ማስረጃዎች</u>፤

1ኛ/<u>ታዋቂው "ኒው ዮርክ ታይምስ" (New York Times) ጋዜጣ</u>፤

ይህ በዓለም-አቀፍ ደረጃ ታዋቂና ታማኝነት ያለው ጋዜጣ፤ እ.ኤ.አ የካቲት 13 ቀን 1937 (February 13, 1937) ስለ ፖፕ ፓየስ 11ኛ ባወጣው ዜና፤ ከዚህ እንደሚከተለው ዘግቧል፤

> "Earlier today the Pontiff had given his recognition of Italian sovereignty over Ethiopia by bestowing his apostolic benediction upon Victor Emmanuel as "King Of Italy and Emperor of Ethiopia." (ትርጉም፤ ቀደም ሲል፤ ዛሬ፤ አቡኑ፤ "ለኢጣልያ ንጉሥና የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት"፤ ለቪክቶር ኢማኑኤል፤ ቅዱስ ቡራኬያቸውን በመስጠት፤ ኢጣልያ በኢትዮጵያ ላይ ስላላት ሉዓላዊነት እውቅናቸውን ገልጸዋል።) ሙሉውን ዘገባ ከዚህ በታች ካለው መመልከት ይቻላል፤
>
> [pius xi.pdf]

2ኛ/ ማንቸስተር ጋርዲያን (Manchester Guardian)

እ.ኤ.አ. የካቲት 12 1929 (February 12, 1929 በወጣው በዚህ ጋዜጣ ዘገባ የሚከተለው ጽሑፍ ይነበባል፤

> "Pope Pius XI is credited with much admiration for Mussolini. That the Italian clergy as a whole are pro-Fascist is easy to understand, seeing that Fascism is a nationalist, authoritarian, anti-liberal, and anti-Socialist force." (ትርጉም፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛ ለሙሶሊኒ ስላላቸው

ከፍተኛ አድናቆት ይነገርላቸዋል። የፋሺሽት ሥርዓት አምባገነናዊ፤ ብሔርተኛ፤ ፀረ-ዲሞክራሲና ፀረ-ሕዝባዊ ኃይል ስለ ሆነ የኢጣልያ ካሕናት በአጠቃላይ የፋሺሽት ደጋፊ መሆናቸውን በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል።)

3ኛ/ **<u>የታሪክ ጸሐፊው፤ አቭሮ ማንሐታን፤ (Avro Manhattan)</u>** "The Vatican in World Politics"፤ (1949) በተሰኘው መጽሐፋቸው፤ በምእራፍ 9፤ ስለ ፖፕ ፓየስ 11ኛ ሲጽፉ፤ (ሙሉውን ምእራፍ በwww.globalallianceforethiopia.org ማየት ይቻላል።

(ሀ) እ.ኤ.አ ከ1922 በፊት፤ ቫቲካንና ፋሺሽቶች ተጻራሪዎች ነበሩ። ከዚያ ዓመት ጀምሮ ግን፤ ቫቲካንና ፋሺሽቶች (ፖፕ ፓየስ 11ኛና ሙሶሊኒ) መቀራረብና መወዳጀት ጀመሩ። በዚሁ መሠረት፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛ፤ "የካቶሊክ ፓርቲ" የተሰኘውን የፖለቲካ ድርጅታቸውን ደመሰሱ።

(ለ) እ.ኤ.አ. በ1926 "Mussolini is the man sent by Providence" (ትርጉም፤ ሙሶሊኒ በፀጋ የተላከ ሰው ነው።) በማለት ሙሉ ድጋፋቸውን በይፋ በመግለጽ የኢጣልያን ሕዝብ የፋሺሽቱን ፓርቲ እንዲደግፍ አመቻቹ።

(ሐ) እ.ኤ.አ. በ1929 ቫቲካንና ሙሶሊኒ፤ "ላተራን" (Lateran) የተሰኘውን ውል ከተፈራረሙ በኋላ፤ ቫቲካን ከፋሺሽቶቹ መጠነ-ሰፊ ገንዘብ ከማግኘቷ በላይ፤ ሕጋዊ እውቅና/ሉዓላዊነትም ለመቀዳጀት ቻለች። በዚህም መሠረት፤ የፖፕ ፓየስ 11ኛና የሙሶሊኒ ወዳጅነት ተጠናከረ። አቭሮ ማንሐታን እንደ ጻፉት፤

> "It was the alliance of these two men, Pius XI and Mussolini, that influenced so greatly the social and political pattern, not only of Italy, but also of the rest of Europe in the years between the two world wars." (ትርጉም፤ የነዚህ የሁለት ሰዎች፤ የፖፕ ፓየስ 11ኛና የሙሶሊኒ ሕብረት ነበር በኢጣልያ ብቻ ሳይሆን በቀረው የአውሮፓ ክፍል ላይ በሁለቱ የዓለም ጦርነቶች መሀል በነበሩት ዓመቶች የማሕበራዊና የፖለቲካ ይዘት ከፍተኛ አጽንኦት ያሳደረው።)

በተጨማሪም፤

> "Thus the Church became the religious weapon of the Fascist State; while the Fascist State became the secular arm of the Church."
> (ትርጉም፤ ስለዚህ፤ ቤተ ክርስቲያኗ (የካቶሊክ) የፋሺሽቱ መንግሥት ሃይማኖታዊ መሣሪያ ስትሆን፤ የፋሺሽቱ መንግሥት ደግሞ የቤተ ክርስቲያኗ ዓለማዊ ክንድ ሆነ።)

(መ)ፋሺሽቶች በኢትዮጵያ ላይ ያከናወኑትን ወረራ፤ የመከላከል ጦርነት መሆኑን ፖፕ ፓየስ 11ኛ ገልጸው ነበር። የፋሺሽቱ ጦር አዲስ አበባ ሲደርስ፤ ከዚህ በታች የተጠቀሰውን የደስታ መግለጫቸውን እ.ኤ.አ. በግንቦት 12 ቀን 1936 በማወጅ፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛ በዚህ ረገድ ከዓለም መሪዎች ከመጀመሪያዎቹ አንዱ እንደ ነበሩ ተረጋግጧል፤

> "The triumphant joy of an entire, great and good people over a place which, it is hoped and intended, will be an effective contribution and prelude to the true place in Europe and the World." (15) (ትርጉም፤ ለአውሮፓና ለዓለም፤ መልካም ጅማሮና ሁነኛ ደረጃ ተገቢ አስተዋጽኦ እንዲሆን ለታቀደና ተስፋ ለተጣለበት ቦታ (ኢትዮጵያን ማለት ነው) የታላቅና ግሩም ሕዝብ (ኢጣልያኖችን ማለት ነው) ከፍ ያለ ደስታ።)

(ሠ)አንዳንድ ካርዲናሎች፤ ለምሳሌ የሚላኖና በሚቀጥለው ገጽ ያለውን መግለጫ ሰጥተው የነበሩት የቱራኖ ጳጳስ፤ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመውን አሰቃቂ የጦር ወንጀል ሲደግፉ፤ በተጨማሪም፤ በፎቶግራፍ ጭምር እንደ ተረጋገጠው፤ የካቶሊክ ካሕናትም ጦሩን ሲባርኩ፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛ ምንም ዓይነት ተቃውሞ ያሰሙት ወይም ያወገዙት ጉዳይ አልነበረም። የቫቲካን መሪ ስለ ነበሩ፤ የበታቾቻቸው ለገለጹትና ላከናወኑት፤ እንደዚህ ለመሳሰለ ከባድ ጉዳይ፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛ ተጠያቂ መሆን እንደሚገባቸው፤ በመንግሥታዊ አሠራር ግልጽ የሆነ ሥርዓት ነው። የቫቲካን ካርዲናሎችና ካሕናት ያበረከቱት ድጋፍና ቡራኬ በግላቸው ስለ ነበር፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛን አያስጠይቃቸውም ማለት፤ ሙሶሊኒ አንድም ጥይት ስላልተኮሰ፤ በኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸመው ጭፍጨፋ ተጠያቂ አልነበረም እንደ ማለት ይሆናል። እንደዚህ ያለ አስተሳሰብ ትክክል ሊሆን አይችልም።

የቱራና፤ የካቶሊክ ካርዲናል መግለጫ፤

> “The war against Ethiopia should be considered as a holy war, a crusade” (as Italian victory would) “open Ethiopia, a country of infidels and schismatics, to the expansion of the Catholic Faith.” (ትርጉም፤ በከሐዲዎቹ ሐገር፤ በኢትዮጵያ፤ የካቶሊክን ሃይማኖት ለማስፋፋት ስለሚጠቅም፤ በኢትዮጵያ ላይ የተፈጸመው ጦርነት እንደ ቅዱስ ጦርነት፤ መንፈሳዊ ዘመቻ መቆጠር አለበት።)

## 4ኛ/ የምሑሩ፤ የዓይን ምስክር፤ የዶር. ሥዩም ገብረእግዚአብሔር ማስረጃ፤

ዶር. ሥዩም፤ በካቶሊክ እምነት ያደጉ፤ በፋሺሽቱ ወረራ ዘመንም፤ ኢትዮጵያ፤ ካቶሊክ ትምሕርት ቤት በመሠልጠን ላይ ይገኙ የነበሩ፤ የዓይን ምሥክር ናቸው። ስለ ፖፕ ፒየስ 11ኛና ስለ ፋሺሽቶች ካጋሩኝ ማስረጃዎች ውስጥ፤ የሚከተለውን እጠቅሳለሁ፤

“In "**The Symphony of my life" published May 2012** I have clearly indicated: as a Catholic Seminarian I was and I am a living witness of the close social, political and economical relations and collaboration of the Church with the Fascist government in Ethiopia. ……… Zwede’s **allegation that Pious 11 did not personally bless Mussolini’s invading army is censored diplomatic journalism not a historian analyses.** Ambassador Zewde has erred, his acceptance of the historical facts so far presented, should convince him to stand up with his fellow Ethiopian in demanding justice.” ትርጉም፡ “ “”The Symphony of My Life” (2012) በተሰኘው መጽሐፌ እንደ ገለጽኩት፤ የካቶሊክ ሠልጣኝ ስለ ነበርኩ፤ (በካቶሊክ) ቤተ ክርስቲያንና ኢትዮጵያ በነበረው የፋሺሽት መንግሥት መሀከል የነበረውን፤ ቅርብ የማሕበራዊ፤ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነትና ሕብረት ያወቅኩና አሁንም የማውቅ፤ የዓይን ምሥክር ነኝ። ………ፓየስ 11ኛ ፤ የሙሶሊኒን ጦር፤ በግላቸው አልባረኩም በማለት ዘውዴ (አምባ.)ያቀረቡት ሀሳብ፤ የታቀበ ዲፕሎማቲካዊ የጋዜጠኛ ዘገባ እንጂ ታሪካዊ ትንተና አይደለም። አምባሳደር ዘውዴ ተሳስተዋል፤ እስካሁን የቀረቡላቸው ታሪካዊ ማስረጃዎች፤ ከኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ጎን ለፍትሕ እንዲቆሙ ሊያሳምኗቸው ይገባል።”

## ድምዳሜ፤

ከላይ በቀረቡት ግልጽ ማስረጃዎች መሠረት፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛና ቫቲካን፤ በኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸመው እጅግ አሰቃቂ ግፍ፤ ተጠያቂ ናቸው። ስለዚህ፤ የቀድሞ አምባሳደር፤ አቶ ዘውዴ ረታ፤ ቃል በገቡት መሠረት፤ “የአጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት” በተሰኘ መጽሓፋቸው፤ የዘገቡትን በማረም፤ ፖፕ ፓየስ 11ኛና ቫቲካን ተጠያቂ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የጽሑፍ መግለጫ በተቻለ ፍጥነት እንደሚያሰራጩ ተስፋ ይደረጋል።

በተጨማሪም፤ ኢትዮጵያውያን ዛሬ በነጻነት የምንኖረው፤ በሰማእቶቻችን መስዋእትነት ስለ ሆነ፤ እስካሁን ያልተቋጨው፤ ለሐገራችን የሚያስፈልገው ፍትሕ እንዲገኝ ሁላችንም በሕብረት ጥረታችንን እንድንቀጥል ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ ነጻነቷንና ክብሯን ጠብቃ ለዘለዓለም ትኑር።